መስከረም ፲፮ ፪ሺህ፲ ዓ.ም

# ዕርቅና ሠላም ወይስ ነፃነትና አርነት፤ አማራጩ ቁልፍ ጥያቄ ለፕሮፈሶር መስፍን ወልደ ማርያም

በአቦ አራዳ አባ ሻውል

ፕሮፈሶር መስፍን ወልደ ማርያም በአሁኑ ሰዓት አዳፍኔ በሚል ርዕስ የጣፉትን መጽሐፍ ብጤ በአሜሪካ እየተዛዛሩ በመሸጥና በማሻሻጥ ላይ የሚገኙ ኤትዮጵያዊ ወይንም ኢትዮጵያዊ[i] (β) ናቸው፡፡ መጽሐፍ  ብጤ ያልኩበት ዋናው ምክንያት በጥናትና በምርምር ያልተደገፈ ታሪክ ካለመሆኑ ባሻገር የዕርቅም ሆነ የሠላም፤ የነፃነትም ሆነ የአርነት ደወልም ሆነ አቅጣጫ ባለማሳየቱ ነው፡፡ የዚህ መጣጥፍ ዓላማ ስለ መጽሐፉ ነቄፈታና ትችት ለማበርከት አይደለም፡፡ ፍላጎቱም ችሎታውም የለኝምና ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ኤርትራ የሚባሉ አገሮች ወዴት እያመሩ እንደሆኑ ምናልባት ፕሮፈሶሩ የሚጠቁምን ዕውቀትም ሆነ ጥበብ ካለ መንፈሳቸውንና ጭንቅላታቸውን በውዘው ሐቁን ቢነግሩን ብየ ነው፡፡ እንማማር በማለት እንጂ እንጻጻፍ ካልንማ መጻፉ ቀላል ነው፡፡ የጥፋት መልእተኛ ካድሬ ተስፋይ ገብረአብ ጽፏል፤ ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ፤ ፍስሐ ደስታ፤ ሁሉም በየአቅሚቲ መጽሐፍ ጽፈናልና መርቁልን እያሉን ነው፡፡ ታዲያ የፕሮፈሰሩ መጽሐፍ ከነዚሁ ብጤው በምን ይለያል፡፡ በዩኒቨርሲቲ አስተማሪነት፤ ለዛውም በዛን ጊዜ ዶክተር መሆንን በማይጠየቅበት ጊዜ ነው፡፡ ለዚህ ለዚህማ አሁን መጽሐፍ እየጻፍን ነው፤ ይኸው ጽፈናል አንብቡልን ግዙን እየተባልን ነው፡፡ ከላይ የጠቀስኩዋቸው ጸሐፊዎች እኮ እኛም ፕሪፈሾሮች ነን ተታግለናል፤ አታግለናል እናም ገድለናል፡፡ ገድለናል ወይንም አስገድለናል የምትለው ቃል ግና አትወጣቸውም፡፡ ለምን ይሆን እቺን ቃል የማይጠቀሙባት ፕሮፈሶሬ? ሊነግሩን ይችላሉ? ወይንስ እኔ ልንገሮዎት፡፡ እንግዲያውስ የመጽሐፍዎ ንዑስ አርዕስት እንዲህ ብሎ አስቀምቶታል  "ፍርሐት እና     "

## ዕርቅና ሠላም

ከዚህ በፊት ዕርቅና ሠላም በሚል መጣጥፌ ዕርቅ የሚመጣው በአገር ወዳዶችና በአብየቶኞች መካከል ሲሆን ሠላም ደግሞ ለለውጥ ሳይታገሉ ያረጁ ሽማግሌዎች እና ሚናቸውን ወይንም ዝርያቸውም -ID- ሆነ አመጣጣቸው በግላጭ ያልተናገሩና የማይናገሩ መካሄድ ያለበት የፖለቲካ ሂደት ነው፡፡ በዛ ጽሑፌ ላይ እንዳስቀመጥኩት ሠላም የሚፈጥሩት አራት ሰዎች ናቸው እነሱም ሦስት ፕሮፈሰሮችና አንድ ታጋይ ማለትም ፕሮፈሰር መስፍን ወልደ ማርያም፤ ፕሮፈሶር በረኸት ሀብተ ሥላሴ፤ ፕሮፈሰር ጌታቸው ኃይሌ እና ታጋይ ስብሐት ነጋ ናቸው፡፡ አራቱም ሰዎች የትምህርት ዕውቀት፤ የመኖር ጥበብና የአስመስሎ መምራት ችሎታ ነበራቸው፤ በአሁኑ ሰዓት ግን ምንም ተሰሚነት ስለሌላቸው ከኅብረተሰቡ ወደ ኋላ ቀርተዋል፡፡ ስለዚህ  ይህን ተገንዝበው እርስ በራሳቸው ሠላም ቢባባሉ ለሚያያቸው ወጣትም ሆነ አዛውንቶች አርአያ ይሆናሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአሁኑ ሰዓት ማለትም በአለቀ ሰዓት ኤርትራ ኢትዮጵያ፤ እስላም ክርስቲያን፤ ወያኔ፣ ኢሕአፓ ማለት አይጠቅማቸውም፡፡ ትዝብትና ጥላቻ ብቻ ነው የሚያተርፉት፡፡ ኑዛዜ ተናዘው ቢያልፉ ነው ለሁሉም የሚሻለው፡፡ ኑዛዜው ምንድን ነው? በሚቀጥለው አርእሰተ-ጉዳይ እናየዋለን፡፡

## ነፃነትና አርነት

ኑዛዜው Freedom + Liberty = INDEPENDENCE የሚለው ቀመር ለእኛ አገር አስፈላጊነት ነበርው ወይ? አሁንስ ቀመሩ ትክክል ነው ወይ ? የመገለጫ ቃላት አሉን ወይ? ወይስ እንደ መልክዓ ምድራችንና ፖለቲካችን ዝብርቅርቅ ያለ ነው? ጥያቄው ሁሉንም አንባቢም ሆነ ቃለ-ሰሚ የሚመለከት ስለሆነ ብንወያይበት መልካም ነገር ነው፡፡ የምሁራኖቹና የታጋዮቹ አለመግባባት በዚሁ የነፃነትና የአርነት ግንዛቤና አመለካከት ላይ ያተኮረ ቅራኔ ስለሆነ ኑዛዜ ያስፈልገናል፡፡

በመሠረቱ ነፃነትና አርነት ምንና ምን ናቸው ብለው ለሚጠይቁ ወጣቶች ፕሮፈሰር መስፍን የሚሰጡት መልስ ከመስፍንነትትና መኳንንት ልዩነትና አንድነት ለይተው የማስረዳት እምነት ያላቸው አይመስለኝም፡፡ እንኳን ረቂቅና ደቂቅ ፅንሰ-ሐሳብና ንድፈ-ሐሳብ የሆነውን ነፃነትና አርነት ቀርቶ በፕሮፌሽናቸው እንካ ማለትም በጂኦግራፊያዊ ሙያቸው፤ መልክዓ ምድርና ፖለቲካዊ ክስተት ልዩነትና አንድነት ሳያስተምሩና በሕዝቡ ዘንድ ሳያስፋፉ የኖሩ የጂኦግራፊ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ተሹመዋል፡፡ እኔ እንደሚገባኝ ፕሮፈሰር መስፍን ከመስፍንነትና መኳንነት ያለፈ ዕምነትና ፍላጎት የነበራቸው አይመስለኝምና ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ መሳፍንትና መኳንንት ሕይወትና ኑሮ ከዘውድ ጋር ሙጢኝ ያለ ሲሆን ዘውዱ (ንጉሡ) በተራው ከፓትሪያርክ ዘንድ ማረኝ ብሎው ሁሉም በአቅሚቲ ተቻችለው የኖሩ ለመሆናቸው የግድ የፕሮፈሰሮች ምስክርነት የሚጠይቅ አየደለም፡፡

የተማሪዎች ማኅበርና የኢሕአፓ ድርጅቶች በዋናነት ዓላማ አድርገው የተነሱት በነፃነትና አርነት ጽንሰ-ሐሳቦችና ንድፈ-ሐሳቦች ላይ ያተኮረ ነበር አሁንም ነው፡፡ ፕሮፈሰር የመሰላቸውና አሁንም የሚመስላቸው ወሎየው ዋለልኝም ሆነ ሸዌው ደብተራው ንጉሡንና ጳጳሱን ከሥልጣን ለማውረድና ሌላ ሰው ለማንገሥ ይመስለቸዋል፡፡ ስለአላስተወሉት ነው እንጂ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ተከታዩን ንጉሥ (225ኛው ንጉሥ) እንዲተኩ አልፈለጉም፡፡ ለውጡንና አብዮቱን ደግፈውታል፡፡ ለዚሁም እንደ ማስረጃ ለሥልሳናቸው አልተዋጉም አላዋጉምም፡፡ ሥልጣናቸውን ለማስረከብ ያሉት ነገር እንደሚከተለው ነበር “ መሪ አላችሁ ወይ፤ የኤርትራ ጉዳይስ? “ ብለው የደርግ ወኪሎችን ጠየቁ ነው ታሪኩ፡፡

ስለሆነም መጻኢው የኢትዮጵያና የኤርትራ እድል በንጉሥነት መጣመር ሳይሆን በፖለቲካል ፓርቲ መስተዳደር እንደሚሆን ሁሉም ተስማምወበት ለውጥ ወይንም በእኛ ቋንቋ አብዮት/ሳውራ ተጀመረ፡፡ በነገራችን ላይ ሃይማኖት ጥያቄ ውስጥ አልገባም አይገባምም ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ በሲኖዶስ ስለሚመራ ለውጥም ሆነ አብዮት አላስፈለገውምና ነው፡፡ አብዮት ስንል የሥርዓት ለውጥ እንጂ የግለ ሰቦች አለመሆኑን ፕሮፈሰሩ አልተገለጠላቸውም፡፡ በራሳቸው አንደበትም አነ ዋለልኝ መልስ ሳይሰጡኝ - እነሱ አላሉም - ግና በፕሮፈሰሩ አባባል “እብድ” ነው ብለው ነው መሰለኝ ትተውኝ ሄዱ ይላሉ፡፡ እኔ እቅጩን ልንገሮዎትና እንኳን በዛን ጊዜ አሁንም አልተገለጠሎትምና በከንቱ ያለፈውን ትውልድ ለማንቋሸሽና ለማኮላሸት መጽሐፍ ብለው ገበያ ላይ አይዋሉ፡፡ ትዝብት ነው ትርፉ፡፡

ለመሆኑ ነፃነትና አርነት ምንድና ምነድን ናቸው ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ያለብኝ ይመስለኛል፡፡ እንዲሁ በጥቅሉ በላቲን freedom እና liberty ሲሆኑ በእኛ ቋንቋ ወይም መዝገበ ቃላት የሉም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ኢትዮጵያ ለብዙ ሺ ዓመታት በነፃነት የኖረች ናት ሲባል ትርጋሜ ለመስጠት ይከብዳል፤ ማለትም በእንግሊዘኛ INDEPENDENCE ለማለት በኢትዮጵያዊነት አይቻልምና ነው፡፡ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደማለት ይቆጠራል፡፡

የኤርትራስ ምንድን ነው የሚባለው ሐርነት ይሆን ነፃነት? መልሱ ሲተገበር በጣም ከፉና አሻሚ ሆኖ እነሆ የኤርትራውያን ዕጣ ፈንታ ስደትና ጸጸት ሆነ ቀረ፡፡ ምክንያቱም ለብዙ ኤርትራውያን በነፃነትና በአርነት ያለው ልዩነትና አንድነት አልተገነዘቡትምና ነው፡፡ ለኤርትራውያን INDEPENDENCE = FREEDOM = LIBERTY ብለው ስለሚያምኑ ቋንቋውም ሆነ ቃላቶቹ የተምታቱ ናቸው፡ ፡

ሪቮሊሲዮን ተብሎ በፈረንሳይ አገር  እ. ኤ. አቆጣጠር በ 1789 ዓም ተጀምሮ ዋናው ዓላማውም LIBERTY, EGALITE et FRATERNITEE ማለትም አርነት፤ እኩልነትና ወንድማማችነት ነበር፡፡ ተገንጣዮችና አስገንጣዮቹ በዚህ መፎከር ትግላቸውን ጀመሩ፡፡ እነሆ ደግሞ ወንድማማችነታቸው ሲያጣላ፤ እኩልነታችን ትርጉም ሳይኖረው ምናላባት በአርነት ልንግባባ እንችል ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡ የኤርትራ ጉዳይ በኢጣልያ ወረራና በአድዋ ላይ መቸነፍ በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን ክፍፍልና ጥላቻ እስከ አሁንም አላበራም፡፡  ጉዳዩም ወደ ማናወቀው አቅጣጫ ወደ አብዮትና ነፃነት ማለትም የሥርዓት ለውጥና ዴሞክራሲ በማለት ተፋጅተናል፡፡ ነገሩ ባልከፋ ይህ ሁላ ችግር ታልፎ ግና ከእንደገና ወደ ጦርነትና ስደት እየመራን እስከመቸ? የአሁኑ አቅጣጫ ደግሞ የከፋ ይመስላል፡፡ ኤርትራ ብሔራዊ እስቴት ፈጥሬአለሁ ስትል፤ ኢትዮጵያ ይከው አለሁ በደቡብ ሕዝቦችና በወያኔ አማካኝነት አዲሲትዋን ወይንም ነባረዋን ኢትዮጵያ እየገነባሁ ነኝ እያሉ ባሉበት ሰዓት ከእንደገና አሥመራ ሄደው በዘር ተቀናጅተው በብሔረ ጉራጌዎችና ጎጃሞች አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ነፃ ልናወጣት ነን ብለው እየፎከሩ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በወላይታ ተወላጅ መሪነት ኤርትራን እመታለሁ እያለ ያሽካካል፡፡ እዚህ ላይ ፕሮፈሰር መስፍን አንድ ይበሉን፡፡ እርሶም ዝርያዎ ይለዩ፤ እንዲሁ በደፋናው ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ነበሩ እየታባሉ እንዳይንገላቱ ወይም እንዳይሞቱ፡፡

## *የመፍትሔ ሐሳብ*

አሁንም የመፍትሔ ሐሳብ ድሮ እነ ዋለልኝ መኮነንና እነ ደብተራው ፀገየ፤ እነ ተስፋዬ ደበሳይና እነ ብርሃነ መስቀል ረዳ፤ እነ ዮሐንስ ስብሀቱና እነ አፈወርቅ ተክሉ የተሰውለትና የተታገሉለት ዓለማ ሕያው ነው፡፡ ነፃነት ሲሉ በዘር፤ በዝርያና በብሕራዊ አመጣጥ ላይ ያተኮረ ነፃነት አልነበረምና፡፡ ማኅበራቸውንና ድርጅቶቻቸው ኢምፐሪያሊዝም ብለው አሜሪካንና ሶቪየት ሩሲያን ሲፈርጁ  በ **RACE**- *ETHNIC*- **NATIONAL ORIGIN** አቃማችውንና ዕምነታችው ላይ ያተኮረ መኖሩን መዘንጋት የለብንም፡፡ **አሜሪካ LIFE**- *LIBERTY*- **PURSUIT OF HAPPINESS** እያለች ለዜጎችዋ እንዴት ለኤትዮጵያውን እኛስ ለምን ይኸንን አንመኝላቸውም በማለት በአመሪካ የነበሩት ኢዙናና ኢናሰአ አገር ቤት ለነበርነው መልዕክቱንና ትምህርቱን አስተላልፈውልናል፡፡ ይኸ ነው እንግዲያ የነፃነት ትረጉምና ምሳሌ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ እንደነ ፕሮፈሰር መስፍን፤እንደነ ፕሮፈሶር በረኸት፤ እንደነ አንድሪያስ እሼቴ እንደነ አማን አንዶም በወጣቱ ክፍል የሲአይኤ ምንደኞች እየተባሉ ያሳለፍንበት ወቅት ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን ሲአይኤና ኬጂቢ አብረው መስራት ከጀመሩ 15 ዓመታት አልፈዋል፡፡ እኛ ግና አሁንም ያው ነው ወይ ፍንክች፡፡ ሴኩሪቲ የሚለው ቃል ለምሁሩ ገና አልገባውም፡፡ ለነገሩ ጃንሆይን በጀኔቭ ላይ ንግግራቸው ኮለክቲቭ ሴኩሪቲ ብለው ደጋግመው ተናግረውት ነበር፡፡ ሰሚ አላጡም፡፡ አሁንም ሰሚ ብናገኝ መልካም ነው፡፡ መስማቱና ስምምነቱ በሦስቱ ፕሮፈሰሮችና በአንድ ታጋይ አእምሮና ልብ እንዲሠረጽ እንጸልይ፡፡ ለነገሩ ፕሮፈሰር እና እኩየቻቸው ጃንሆይን በእንግሊዘኛ ቋንቋ SENILE ሆኑ ይሉን

ነበር ነገሩ ሳይገባን ዝም ብለን እንቀበላቸው ነበር፡፡ አሁን ግና እነሱም ጃጁ፤ ሲኒየር ሲሪዝን ሆኑ፤ ዲዝአብል ሆኑ መኖሪያቸውም ተደኅመላቸው፡፡ አርነትን ተኀናጠፉ፡፡አብየት የባሕል ለውጥ ማለት! እንዲያ ነው፡፡ የፕሮፌሶር ልጅና ኤርትራዊው ሲጋቡ ተፈጠመ ጉዳዩ፡፡ ዕድሜ ዘልዛላ ነው እንዲሉ እነሆ እያየነው፡፡

የሐሳብ መፍትሔውን ለማፋጠን ፕሮፌሶር መስፍን ወልደ ማርያም ምርጫቸው በሁለቱ አማራጭ እንዲያቶክሩ እንማጸናለን፡፡ ማደፍረስና ማፍረስ ቀላል ባይሆንም መገንባት ደግሞ የበለጠ ከባድ ነው፡፡ ያለፈውን ትውልድ ለመናድ ለእርስዎ ጭንቅላት ከባድና ውስብስብ ነው፡፡ለሩጫዎ መኻለቅ ያብጁለት፡፡ ወጣቱ ትውልድ ነፃነትና አርነት አግኝቶ፤ ተደራጅቶ ኑሮውን ወደፊት እንዲያሻሻልለት እንጂ እንዲሁ በአታካሮ ትግልና ኑሮ (አርአያነት የሌለው) እዚህም እዚያም እየረገጡ መኖር አክትመዋል፡፡ lone wolf መሆን ለግልዎ ያዋጣል፤ ነገር ግን ሕዝብን ለማስተማርና ለመምራት አያዋጣም ፡፡ ለአገርም ለዓለም አቀፍ ጆግራፊም አይበጅም፡፡ ይሉቅንስ ከአቻቻዎ ማለትም ከዶክተር በረኸት፤ ፕሮፌሶር ጌታቸው ኃይለና ከታጋይ ስብሐት ነጋ ሰላም ፍጠሩ፡፡ ዕረቁ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለኤርትራ ሕዝብ ተዉለት፡፡ እኛ የምንጠይቀው ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ሺ ሰማንያ እንዲከፈት ብቻ ነው፡፡ ሕዝቡን በጆግራፊ ክልል አስራችሁ፤ የቋንቋ ልዩነት ፈጥራችሁ፤ የሃይማኖት አቅጣጫ እያሳያቹ ወደ ሌላ ጦርነት አታዘጋጁን፡፡ እዚህ ላይ ፕሮፌሶር መስፍንን በማከፋፈል ደረጃ አልፈረጅኩም ነበረ ሆኖም በቅርብ ቀን ኤሪትራዊ ሆነው ስቀረቡ ገረሞኝ ነው፡፡ የኤርትራ ባንዴራ ወክለው ቀረቡሳ? በደህና ነው? የSENILE ጊዜው ደርሶ እንዳይሆን!!!

ወቀሳም ሆነ ሒስ በሚገባ አስተናግዳለሁ

mailto:oboaradashawl@gmail.com

---

[i] Race = ኤርትራዊ
Ethnic = ኢትዮጵያዊ
National Origin = ኤትዮጵያዊ